# ቢርፕሌን (Bearplane)!




## የአር አይ ኤፍ (RIF) መምሪያ ለቤተሰቦች

ይዘቶች (Themes)፤ ቤተሰብ፤ መጓጓዣ (Transportation)፤ ጉዞ (Travel)

የመጽሃፉ አጭር መግለጫ (Book Brief)፤ አንድ ትንሽ ድብ ሻንጣቸውን ጠቅልሎ ከአብሮ-አደጉ ጋር በመሆን ለመጀመሪያ በረራቸው ወደ አየር መንገድ አመሩ። ሁለቱ በአየር መንገዱ ውስጥ ብዙ ቦታዎችን በማለፍ አያት ለመጠየቅ ወደሚያደርጉት ልዩ በረራ መግቢያ በመድረስ በረራ ጀመሩ።

ደራሲ፤
ዲቦራህ አንደርዉድ
(Deborah Underwood)

ሰዓሊ፤
ሳም ወደሊች
(Sam Wedelich)

## የማንበብ ጊዜ!



ከንባብ በፊት፤ የታሪኩን ርዕስ ያንብቡ እና ሽፋኑን ይመልከቱ። ድቡ የት እንዳለ ልጅዎን ይጠይቁ? እንዲህ እንዲያስቡ ያደረጋቸው ምንድን ነው?

በንባብ ጊዜ፤ በሚያነቡበት ጊዜ ልጅዎ በሥዕሉ ላይ ሲፈጸሙ ስላየው ነገር ሁሉ ለሌሎች እንዲያካፍል ያድርጉ። "ትንሹ ድብ ምን እየሰራ ነው? ትንሹ ድብ አሁን ምን ይሰማዋል?" በማለት ይጠይቁ።

ከንባብ በኋላ ጥያቄዎች ይጠይቁ፤

- ትንሹ ድብ በአውሮፕላን ለመጓዝ ማድረግ የነበረበት ነገር ሁሉ ምንድነው?
- በአውሮፕላኑ ውስጥ ባደረገው ጉዞ ሁሉ የትንሹ ድብ ስሜት የተለወጠው ለምንድን ነው?
- በአውሮፕላን ጉዞ ወዴት ትሄዳለህ? ለምን ወደዚያ ትሄዳለህ?

## ውይይት ጀማሪዎች (CONVERSATION STARTERS)

ጽሁፎችን እንደገና ማንበብ ለጀማሪ አንባቢዎች ጠቃሚ ልምድ ነው። ተወዳጅ መጽሃፎችን እንደገና መጎብኘት አስደሳች ነው፣ እና ትናንሽ ልጆች ስለ ታሪክ ጥልቅ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ይረዳል። በድጋሚ በማንበብ፣ በጽሁፉ ውስጥ አዲስ ዝርዝሮችን ወይም መጽሐፉን አስደሳች ወይም አስቂኝ የሚያደርጉትን ምሳሌዎች ትኩረት መስጠት ይችላሉ። መጽሐፍን እንደገና ማንበብ ልጆች በታሪኮች ውስጥ ካሉ ገፀ-ባህሪያት ጋር ያላቸውን ግንኙነት እንዲያዳብሩ እና ዝርዝሮችን በራሳቸው ተሞክሮ ውስጥ ካሉ ክስተቶች ጋር እንዲያዛምዱ ይረዳቸዋል። ቢርፕሌን (Bearplane)! በጽሁፉም በስዕሉም ብዙ ዝርዝሮች ያለው መጽሐፍ ነው። ታሪኩን ደጋግመው ሲያነቡ፣ ከልጅዎ ጋር ሊወያዩበት እና ሊመለከቱት የሚችሏቸው አዳዲስ ነገሮችን ሊያስተውሉ ይችላሉ። ለምሳሌ፣ በሁለተኛው ወይም በሦስተኛው ንባብ ወቅት፣ በታሪኩ ውስጥ ባለው ጨካኝ ድብ ላይ ምን እንደሚፈጠር ልዩ ትኩረት መስጠት ትችላለህ። የሚያውቋቸውን እና የሚወዷቸውን መጽሃፎችን እንደገና በመመልከት ልጅዎ በማንበብ እንዲደሰት እርዱት!

## ተዛማጅ ተግባራት

**ደረጃ በደረጃ**

የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶች፤ ወረቀት እና ሰዕል ለመሳል እና ለመጻፍ እንደ ክራዮንስ ወይም ማርከር ያሉ ነገሮች

በቢርፕሌን (Bearplane)! ውስጥ ትንሹ ድብ በአውሮፕላኑ ላይ ለመብረር ብዙ ደረጃዎችን መከተል አለበት። ታሪኩን ካነበቡ በኋላ፣ ልጅዎ ከታሪኩ ውስጥ ጥቂት (ከሦስት እስከ አምስት) ክስተቶችን እንዲስል ያድርጉት። ስዕሎቹን ስሎ ከጨረሰ በኋላ ይደበላልቋቸው እና ከታሪኩ አንጻር በቅደም ተከተል እንዲደረድራቸው ያድርጉ።

በቅደም ተከተል መደርደሩን ለማገዝ መጽሐፉን መለስ ብለው ይመልከቱ ወይም በራሱ በትክክል ያገኘው መሆኑን ያረጋግጡ!







## ተጨማሪ ሪሶርሶች(RESOURCES)



**ስለ አውሮፕላኖች ሌሎች መጻህፍት**

- ዘ አልትሜት ቡክ ኦፍ ኤየርፕሌንስ ኤንድ ኤየርፖርትስ (The Ultimate Book of Airplanes and Airports) (2017)
- ዞየስ ፈርስት ፕሌን ራይድ (Zoey's First Plane Ride) (2017)
- ኤየርፕሌንስ፤ ሶሪንግ! ዳይቪንግ! ተርኒንግ! (Airplanes: Soaring! Diving! Turning!) (2012)

©2024 Reading Is Fundamental

Reading Is Fundamental | Read for Success Early Childhood